

# የኢየሱስ ጥምቀት

❈ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሰዎችን ያጠምቅ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት መጣና ዮሐንስን እንዲያጠምቀው ጠየቀው። ዮሐንስ ግን ተቃወመው። እንዲህም አለው “እኔ በአንተ መጠመቅ ሲገባኝ እንዴት እኔ እንዳጠምቅህ ትጠይቀኛለህ?” ኢየሱስ ግን የሚጠመቅበት ምክንያቱ ፅድቅን ሁሉ መፈፀም ስላለበት እንደሆነ ለዮሐንስ ገለፀለት። ስለዚህም ዮሐንስ ኢየሱስን በወንዙ ውስጥ አጠመቀው። ልክ ኢየሱስ ተጠምቆ ከወንዙ ወጥቶ እየፀለየ ሳለ ሰማያት ተከፈቱ። እርግብም ወርዶ በላዩ ላይ አረፈበት።

❈ በእርግብ መልክ በኢየሱስ ላይ ያረፈው መንፈስ ቅዱስ ነበር። ይህም ለኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት አንዱ ማስረጃ ነበር።

❈ ወዲያውም “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው። እርሱን ስሙት።” የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ። ድምፁና እርግቡ ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ እንዲያውቅ ለዮሐንስ ምልክት ነበር።

❈ ከዚህ በኋላ ዮሐንስ በአጠገቡ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው በነበሩበት ወቅት ኢየሱስ በመካከላቸው ተገኘ። ዮሐንስም ከበውት ለነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ሲወርድበት እንዳየና ይህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠው ምልክት እንደነበር ገለጠላቸው። ኢየሱስና ዮሐንስ ዘመዳሞች ነበሩ። እድገታቸውም በአንድ ላይ ነበር። ኤልሳቤጥ የዮሐንስ እናት ኢየሱስ ክርስቶስ ገና ሳይወለድ ዘመዷ ማርያም ለእግዚአብሔር ልጅ እናት እንደምትሆን ታውቅ ነበር። ኢየሱስ በሰው መልክ ወደምድር የመጣው እግዚአብሔር ነው። ሆኖም ዮሐንስ በዚህ በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት ምልክቶችን እስኪያይ ድረስ የኢየሱስን እውነተኛ ማንነት የተረዳ አይመስልም።

- ዮሐንስ ግን ወደአለም ለሚመጣው ክርስቶስ መንገድን የማዘጋጀት ተልእኮ ነበረው። ተልእኮውንም በሚገባ እየተወጣ ነበር። አሁን ክርስቶስ ተገልጦአል።

- አንዳንድ ሰዎችም ወደ ዮሐንስ መጡና ከእርሱ ይልቅ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን እየተከተሉት እንደሆነ ነገሩት። እነርሱም ዮሐንስ ይህን ሲሰማ የሚበሳጭ መስሏቸው ነበር። እሱ ግን ምንም አልመሰለውም።
  ይልቁን እርሱ እራሱ ክርስቶስ ያለመሆኑን ከዚህ በፊት እንደነገራቸው አስተወሳቸው። ክርስቶስ እንደ ሙሽራ እርሱ ደግሞ እንደሚዜ እንደሆነ ገለጠላቸው። ሰዎች ክርስቶስን መከተል በመጀመራቸው ደስተኛ እንደሆነም ነገራቸው። በተጨማሪም ክርስቶስ ከፍ ሊልና እርሱ (ዮሐንስ) ግን ዝቅ ሊል እንደሚገባው አስረዳቸው።

*የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3:13-17 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com